“በዚያን፡ጊዜ፡መንግስተ፡ሰማያት፡መብራታቸውን፡ይዘው፡ሙሽራውን፡ሊቀበሉ፡የወጡ፡ አሥሩ፡ቆነጃጅቶችን፡ትመስላለች።” (ማቴ፡ምዕ፡25፤1)

# <u>አሥሩ፡ቆነጃጅቶች</u>

አምስቱ፡ተጠንቅቀው፡
አምስቱ፡ችላ፡ብለው፤
አምስቱ፡ሻማ፡ይዘው፤
አምስቱ፡ባዶ፡እጅ፡ሆነው፤
አምስቱ፡ልብ፡አድርገው፤
አምስቱ፡ደክመው፡ዝለው፤
የአምስቱ፡ማሰሮ፡ዘይት፡ሞልቶ፤
የአምስቱ፡ግን፡ባዶ፡ቀረቶ፤
የአምስቱ፡መብራት፡በርቶ፤
የአምስቱ፡የለም፡ጠፍቶ፤
አምስቱ፡በርትተው፡ቆመው፤
አምስቱ፡በእንቅልፍ፡ተሸንፈው፤
በድንገት፡ሙሽራው፡መጣ፤
ያላስቀመጡት፡ከየት፡ይምጣ፤
አምስቱ፡የተሰናዱት፤
ወጡ፡ሙሽራውን፡ሊቀበሉት፤
አምስቱ፡ደንግጠው፡ፈርተው፤
ዘይት፡ለመግዛት፡ተሯርጠው፤
አጥተው፡ሲመለሱ፡በጣም፡አዝነው፤
ሙሽራው፡ገብቶ፡ጠበቃቸው፤
በሩ፡ተዘግቶ፡ከፊታቸው፤
አምስቱ፡ከውስጥ፡ያሉት፤
ከሙሽራው፡ጋር፡የከበሩት፤
እነሱ፡ናቸው፡የተጠሩት፤
ቀንና፡ሌሊት፡ተግተው፡የጠበቁት።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ፡ (ለንደን)
መጋቢት፡2001